# የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

**Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)**

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com


## መፍትሄው በብሄራዊ መግባባት የሽግግር ሂደትን እውን ማድረግ እንጂ ለ27 ዓመት የተደረገውን መድገም አይደለም

ታህሣስ 22፣ 2010 (December 31, 2017)

በትላንቱ ዕለት ህወሓት-መራሹ የኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ 17 ቀናት የወሰደ ስብሰባውን እንዳጠናቀቀ በማመልከት መግለጫ አውጥቷል። ስብሰባው ከመጠናቀቁ በፊት ትልቅና አዲስ ነገር አመላካች የሆነ ውሳኔ እንደሚያስተላልፍ በተለያየ መልክ ሲጠቁም ቢከርምም፣ የመጨረሻው መግለጫ እንደሚያመለክተው ግን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ካለፉት ጊዜያት የተለየ ተስፋ ሰጭ ነገር ይዞ አልመጣም።

ይህ ደግሞ ሀገራችን ባለችበት ሁኔታና ሕዝባችን ለመብቱ መከበር እያሳየ ከሚገኘው ቆራጥነት አንፃር ሲታይ ገዥው ህወሓት-መራሹ ኢህአዴግ አሁንም ለሕዝባችን ብሶት፣ ለሀገር ደህንነትና ለአካባቢውም መረጋጋት ደንታ እንደሌለው፤ ከዚያም አልፎ ሥልጣኑን ይዞ ለመቆየት ደግሞ አፈናውን፣ ረገጣውን፣ ከፋፋይነቱን ባጠቃላይም ከፍተኛ ወንጀልን ከመፈጸም እንደማይመለስ አመላክቷል።

የኢህአዴግ መግለጫ አገዛዙ የዴሞክራሲ መብቶችን እንዳፈነ፣ የህግ የበላይነትን እንደጣሰ፣ የሲቪክ ማኅበራት እንዳይኀለብቱ አንዳደረገ፣ የመደብለ ፓርቲ ሥርዓት ግንባታን ማመቻቸት ሲገባው እንዳፈነ፣ ሰላምንና በሕዝባችን መካከል መፈቃቀርን ማምጣት ሲገባው ጭራሹን ሀገራችን በታሪኳ ታይቶ ወደማይታወቅ የእርስ በርስ ግጭት አንድታመራ እንደሆነ፣ ሙሰኛነትን አንዳነገሰ፣ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደህንነቱ እንደተናጋ ከመኖሪያው እንደተፈናቀለ...ወዘተ ተናዟል።

ይህ ማለት አገዛዙ በማንኛውም መመዘኛ ቢታይ እንደመንግሥት ሀላፊነቱን አልተወጣም ብቻ ሳይሆን በሀገሪቱ ውስጥ ለሚታየው ታላቅ ምስቅልቅልና ቀውስ ዋናው መሠረቱ እንደሆነ ያረጋግጣል።

ሀላፊነት የሚሰማውና ተጠያቂነት ባለበት ሥርዓት ውስጥ ለ27 ዓመታት በሥልጣን ላይ ቆይቶ ሀገርን ወደዚህ ዓይነት ቀውስ ያስገባ አገዛዝ ሥልጣኑን ወዲያውኑ መልቀቅ ይገባዋል። ለሕዝብ ተጠያቂ መሆን ማለት ይህ ነው። በህወሓት-መራሹ የኢህአዴግ አገዛዝና ሥርዓት ግን ሁኔታው የተገላቢጦሽ ነው። ጥፋቱን እያመነ፣ የሠራውን በደል እያመነ መንግሥታዊ ስልጣኑን ግን ይገፎ መቀጠል ያለብኝ እኔው ነኝ ይላል። ከሕዝብ ፍላጎት ውጭ አሁንም በሥልጣን ላይ እቆያለሁ ይላል። ይህ ከሀገርና ከሕዝብ ይልቅ ሥልጣኑን ምን ያህል እንደሚወድና በሥልጣን ኮርቻ ላይ ሙጭጭ ብሎ ለመጓዝ ምን ያህል እንደቆረጠ ማረጋገጫ ነው። ይህ ሀላፊነት የጎደለው ህሊና ቢስነት፣ አሳፋሪ ብቻ ሳይሆን አሳዛኝም ነው።


Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : shengo.derbiaber@gmail.com

የደንቆሮ ለቅሶ መልሶ መልሶ እንደሚባለው ህወሓት-መራሹ ኢህአዴግ አሁንም “አታደሳለሁ፣ እለወጣለሁ ጊዜ ስጡኝ” ቢልም 27 ዓመት ራሱን ለማስተካከል በቂ ጊዜ እንደነበር ማንም የሚገነዘበው ነው። ስለዚህ በጉልበትና በአመጽ አገዛዙን ለመቀጠል ይጥራል እንጂ ከዚህ በኋላ ከሕዝብ ምንም ዓይነት ድጋፍ ሊያገኝ ከቶ አይችልም።

ህወሓት-መራሹ ኢህአዴግ በማስፈራራትም ሆነ በሌላ የከሰረና የተጠላ አገዛዙን መልሶ በሕዝብ ላይ ለመጫን የሚያደርገው ሙከራ አሁን ከሚታየው እጅግ የበዛና የጠነከረ የሕዝብ ተቃውሞን መቀስቀሱ አይቀሬ ነው። ይህ የሚሆነው ደግሞ በ27 ዓመት ጉዞው ሕዝብ ሥርዓቱን በሁሉም መልኩ ጠንቅቆ ስለሚያውቀውና በዚህ ሥርዓት ሥር ለመኖር ፈጽሞ ፈቃደኛ ስላልሆነ ነው።

የሕዝቡ ጥያቄ ህወሓት-መራሹ አገዛዝ እንዲሻሻል ሳይሆን፣ የ27 ዓመት የግፍ አገዛዝ እንዲያበቃ፣ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ ፍትሕ እንዲሰፍን የፖለቲካ እሥር እንዲያበቃ፣ የመናገር፣ ሰልፍ የማድረግ፣ መሪዎቹን በራሱ ፍላጎት በነፃ መምረጥ እንዲችል፣ መሬት ነጠቃው እንዲቆም አድልዖ እንዲያበቃ በአግዓዚና በልዩ ኃይል መደብደቡና መገደሉ እንዲያበቃ ሙሉ መብቱ አንዲረጋገጥ ነው። በመሆኑም መሠረታዊ ጥያቄው እስካልተመለሰ ድረስ ትግሉ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ማወቅ ተገቢ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) ደግሞ ደጋግሞ እንደገለጸው ሀገራችንና ሕዝባችን አሁን ከሚገኙበት ምስቅልቅል ወደ ዴሞክራሲያዊና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ማሸጋገር እጅግ አጣዳፊ ተግባር ነው። የሀገራችን ችግሮች ዋናው መሠረት የሆነው ህወሓት-መራሹ የኢህአዴግ አገዛዝ፣ ችግሩን ተንታኝ መፍትሂውንም ጠቋሚ፣ መፍትሂውንም ተግባራዊ አድራጊ ሊሆን ከቶ አይችልም። ይህን ማድረግ የሚታየውን ቀውስ ይበልጥ ማወሳሰብ፣ የሕዝባችንንም ስቃይ ለመራዘም መሞከር ነው።

መፍትሂው ሁሉን አቀፍ ብሄራዊ መግባባትና የሽግግር ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ ለሀገራችን ውስብስብ ችግሮችም በሆደ-ሰፊነትና ከቂም በቀል ነፃ በሆነ መንገድ ሀገራዊ ዕርቅን ተግባራዊ ማድረግ ነው። ይህንንም በማድረግ የፖለቲካ ቀውስንና አዙሪት መስበር ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማኅበራትና ያገባናል የሚሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ተባብረን ትግሉን መቀጠል የሕዝባችንንም ትግል ይበልጥ የተቀነባበረና ባጭር ጊዜ ውስጥም ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ አበክሮ መታገል ነው።

በዚህ ሂደት ውስጥ የመከላከያ ኃይሉም ይሁን በኢህአዴግ ውስጥ የሚገኙ ለውጥ ፈላጊዎች ሁሉ ትግላችን የሁሉንም ኢትዮጵያዊ መብት የሚያስከብር፣ ሁሉንም አኩሪና አሳታፊ የሆነ ህገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እውን ለማድረግ እንደሆነ ተገንዝበው ከትግሉ ጎን እንዲቆሙ ጥሪ እናቀርባለን። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም አላስፈላጊ የሆነ የእርስ በርስ ግጭትን ማስወገድ የሁላችንም ሀላፊነት በመሆኑ ማንኛውንም ከፋፋይና ተንኳሽ ሤራ ለማክሸፍ ነቅተን እንድንቆም ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የሕዝባችን ስቃይ እንዲያበቃ ትግላችን ተጠናክሮ ይቀጥል!

Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : **shengo.derbiaber@gmail.com**